# የመማር ማስተማር ተግባር ከተማሪዎች ባህርይ ጋር እንዴት ማጣጣም ይቻላል?

ከዳንኤል ደስታ

በዚህ አጭር ጽሁፍ ባህርይ የሚለዉ ቃል የተማሪዎችን ችሎታ፥ ስሜትና ፍላጎት ከደካማና ጠንካራ ጎኖቻቸዉ ጋር አገናዝቦ ለመግለጽ የገባ ነዉ። የትምህርትን ስራ ከተማሪዎች ባህርይ ጋር በተገናዘበ መልኩ ማካሄድ ለዉጤታማነት እንደሚያግዝ ይታመናል። በዕድሜና በልምድ እየዳበረ የሚሄደዉ የልጆች የትምህርት አቀባበል ችሎታ በመማር ማስተማር ሂደት ግንዛቤ ዉስጥ መግባት ያለበት አብይ ጉዳይ ነዉ። የልጆች የትምህርት ፍላጎት ከአካባቢ ሁኔታዎች፥ ከአካልና ከአእምሮ መዳበርና መበልፀግ ጋር በቅርብ የተያያዘ መሆኑን ማጤን አስፈላጊ ነዉ። ከዕድሜና ከእድገት ጋር የመለዋወጥ ባሕርይ ያላቸዉ የልጆች አካላዊ፥ አእምሮአዊ፥ ስሜታዊና ማኅበራዊ ብስለትና ብቃት ሁልጊዜ በትምህርቱ ሂደት መካተት ይኖርባቸዋል። ከዚህ መሠረታዊ ጉዳይ አኳያ አንድ መምህር መቼ ምን ማድረግ እንዳለበት ከስልቶቹ ጋር ለይቶ ማወቅ ይጠበቅበታል። ይህ ጽሑፍ በተለይ ዕድሚያቸዉ ከ20 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችንና ወጣቶችን ባህርይና ተጓዳኝ የትምህርት አቀራረብ ስልቶች ለመምህሩ ለመጠቀም ይሞክራል። ጽሑፉ ዝርዝር ጉዳዮች ዉስጥ የማይገባ ቢሆንም ዋና ዋና ነጥቦችን ጠቅለል ባለ መልክ በማቅረብ ለመምህራን አንዳንድ ሀሳቦችን ይጠቁማል።

## ልጆች ፈጣን አካላዊና አእምሮአዊ እንቅስቃሴ ዝንባሌ አላቸዉ

ልጆች በተፈጥሮአቸዉ ፈጣን አካላዊና አእምሮአዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ከፍተኛ ፍላጎትና ዝንባሌ ያሳያሉ። መዝለል፥ መሮጥ፥ መጣል፥ ማንሳት ወዘተ ያዘወትራሉ። ይህም ለአካላዊና ለአእምሮአዊ መዳበር አስተዋጽኦ ይኖረዋል። እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ እያላቸዉ በክፍል ዉስጥ ለረዥም ጊዜ ያለአንዳች አካላዊ እንቅስቃሴ መቀመጥን አይወዱም። እንዲቀመጡ ከተገደዱም በትምህርቱ ሂደት የሚኖራቸዉ ተሳትፎ ዉሱን ይሆናል። ይህ ለአብዛኛዉ ተማሪ የሚሰራ አጠቃላይ እዉነታ ከሆነ መምህሩ ከዚህ ምን መማር ይችላል? የመማር ማስተማር ሂደቱንስ እንዴት ማመቻቸት ይኖርበታል?

ልጆች ከአንድ ሰዓት የበለጠ ጊዜ እንደሁኔታዉ እስከ 3 ሰዓት ያለምንም አካላዊ እንቅስቃሴ በክፍል ዉስጥ ተቀምጠዉ እንዲማሩ የሚደረግ መሆኑ ይታወቃል። ይህ ለረጅም ጊዜ የመቀመጥ ሁኔታ ከልጆች አካላዊና አእምሮአዊ ባሕርይና ፍላጎት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ድካምንና መሰላቸትን ማስከተሉ አይቀርም። በመሆኑም በትምህርት ሂደት ዉስጥ ንቁ ተሳትፎ ላይኖራቸዉ ይችላል። በትምህርት ሂደት በንቃት የማይሳተፉ ተማሪዎችን ለይቶ ማወቅና ማበረታታት ከመምህሩ ከሚጠበቁ ተግባሮች አንዱ ነዉ። ይህንን ችግር ለማቃለል የግዴታ ተማሪዎችን ከክፍል ማስወጣት አያስፈልግም። በተለይ ተማሪዎች ለአንድ ፔሬድ ወይም ለበለጠ ጊዜ ክፍል ዉስጥ ተቀምጠዉ የነበሩ ከሆነ አዲስ ክፍለ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት እንዲቆሙና በያሉበት ሰዉነታቸዉን እንዲያፍታቱ ማድረግ ጠቃሚ ነዉ። ማዛጋት፥ ወንበር ላይ ረግቶ አለመቀመጥና

መቁነጥነጥ፣ ፀጉር ማሻሸት፣ ወዘተ ምልክቶች የተማሪዎችን የመሰላቸት ሁኔታ ይጠቁማሉ። አንድ መምህር ከማስተማሩ ሥራ ጎን ለጎን የእነዚህ ችግሮች መከሰት በንቃት መከታተል ይጠበቅበታል። በክፍል ዉስጥ የድካምና የመሰላቸት ሁኔታ የሚታይባቸዉን ልጆች በመጥራት ጥያቄ እንዲመልሱ በማድረግ፣ ደብተራቸዉን ለመምህሩ እንዲያሳዩና አስፈላጊ ከሆነም እንዲያሳርሙ በማድረግ፣ እንደአስፈላጊነቱ የሌሎችን ተማሪዎች ደብተር ሰብስበዉ ለመምህሩ እንዲሰጡ በማድረግ ከድካምና መሰላቸት መንፈስ እንዲላቀቁ ማድረግ ይቻላል። እንደአስፈላጊነቱ በክፍለ ጊዜዉ መካከል የክፍሉ ተማሪዎች በሙሉ እንዲቆሙና ሰዉነታቸዉን እንዲያፍታቱ ማድረግ ይቻላል።

## ልጆች ማህበራዊ ግንኙነት የማዳበር ፍላጎት አላቸዉ

ልጆች ለወደፊቱ ኑሮአቸዉ የሚያስፈልገዉን የማህበራዊ ግንኙነት ስልት ለማዳበርና እርስ በርስ ለመማማር፣ ለመተዋወቅና ለመረዳዳት ካላቸዉ ፍላጎት የተነሳ የቡድን ሥራ ዝንባሌ ያሳያሉ። ይህ ጤናማ ዝንባሌ ለመምህሩ ሥራ ምን ትርጉም ይኖረዋል? መምህሩ የተማሪዎችን የቡድን ሥራ ፍላጎት ከትምህርቱ አቀራረብ ጋር እንዴት ማገናዘብ ይኖርበታል?

ተማሪዎች በቡድን የመስራት ፍላጎት እንዳላቸዉ ከተገነዘብን የቡድን ሥራዎችን ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ ለትምህርቱ ዉጤታማነት ያግዛል። የሂሳብ ፕሮብሌሞችን፣ የሌሎችን ትምህርቶች መልመጃዎችን፣ ዉይይቶችን፣ የጽዳት ዘመቻ ስራዎችን፣ ወዘተ በቡድን እንዲሰሩ ማበረታታት ጠቃሚ ነዉ። የቡድን ስራ አንዱ ከሌላዉ እንዲግር ከማገዙም በላይ ልጆች ከመሰሎቻቸዉ ጋር በመቀራረብና በመወያየት ሀሳብ መግለጽንና መቻቻልን እንዲለምዱ ይረዳል። ቡድኖች ለጥናት ወይም ለሌላ ተግባር ሲዋቀሩ አባሎቻቸዉ በመምህሩ እገዛ በጥንቃቄ መመረጥ ይኖርባቸዋል። የቡድን አባላት ከቡድን ሥራ እንዲጠቀሙ ከተፈለገ መምህሩ በየጊዜዉ የቡድኑን ሥራ ዉጤትና የአባላቱን ተሳትፎ በቅርብ መከታተልና መገምገም ይኖርበታል። እንደአስፈላጊነቱም አባላትን ከአንድ ቡድን ወደ ሌላዉ በድን ማዘዋወር ጠቃሚ ይሆናል።

## ልጆች በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትንና መወደድን ይፈልጋሉ

ልጆች በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ እንደመሪያቸዉ በሚያዩዋቸዉ አስተማሪዎቻቸዉና ወላጆቻቸዉ ዘንድ በአድናቆት መታየት፣ መወደድንና መታወቅን ይፈልጋሉ። በጓደኞቻቸውም ዘንድ እንዲሁ። በአንጻሩ ደግሞ ነቀፌታንና ጥላቻን አይወዱም። ይህ ለአብዛኛዉ ልጅ የሚሰራ አጠቃላይ እዉነታ ከሆነ መምህሩ የዚህ ዓይነቱን የተማሪዎች ፍላጎት ጠብቆ የትምህርቱን ሂደት እንዴት መምራት ይገባዋል?

ልጆችን በስማቸዉ ለይቶ ማወቅና መጥራት፣ በክፍል ዉስጥና ከክፍል ዉጭ በግልም ሆነ በቡድን የሚሰሩትን ትምህርት ነክ ሥራዎች ማበረታታትና መልካም ዉጤቶችን ማድነቅ ጠቃሚ ነዉ። ይህ ልጆች ስለራሳቸዉ ያላቸዉን ግንዛቤ ቀናና ጠንካራ ከማድረጉም በላይ ለወደፊት ሥራቸዉም ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ ይሆናል። በተጻራሪዉ ግን ልጆች ከተነቀፉ፣ ከተናቁ፣ ከተሰደቡ፣ ወዘተ ስለራሳቸዉ የሚኖራቸው ግንዛቤ ቀና

ካለመሆኑም በላይ ስለሌሎች ሰዎች ስለትምህርትና በአጠቃላይ ስለኑሮ የሚኖራቸዉ አመለካከት የተዛባና ጎጂ ሊሆን ይችላል።

ልጆች ለጓደኞቻቸዉ ለወላጆቻቸውና ለአስተማሪዎቻቸዉ ጠቃሚ አገልግሎት በመስጠት እርካታንና ደስታን ያገኛሉ። ለዚህ ዓይነቱ ተግባር ዕድል መስጠት በጣም አስፈላጊ ነዉ። ለምሳሌ በተለያዩ ኮሚቴዎች ሥራ በአባልነት በመሳተፍ በአትክልት ተከላ፥ ለአትክልት ዉኀ በማጠጣት፥ በጽዳት ሥራ ዘመቻዎች ቢሳተፉ ደስታን ከማግኘታቸዉም በላይ ሥራቸዉ ጠቃሚና ተፈላጊ መሆኑን በመረዳት ስለራሳቸዉ ቀና አመለካከት ያዳብራሉ።

## ልጆች ነፃና ተጽዕኖ የሌለበት የትምህርት አካባቢ ይፈልጋሉ

ልጆች በተፈጥሮ በነፃነት የመንቀሳቀስ፥ የመጠየቅ፥ የመመራመር ፍላጎት አላቸዉ፤ ነፃነት የሌለዉ በቁጣና በማስፈራራት የተሞላ የመምህር ግንኙነት ልጆቹን ከማስደንገጡም በላይ የማሰብንና ጠይቆ የመረዳትን ዝንባሌ ሊቀንስ ወይም እንደሁኔታዉ ሊገታ ይችላል። ሁኔታዉ ከተደጋገመ የልጆቹን ብቃትና ማኅበራዊ ግንኙነት ይጎዳል። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት መምህሩ ምን ማድረግ ይገባዋል?

በትምህርት ሂደት ዉስጥ ወሳኙን ሚና መጫወትና በአካልም በአእምሮም በቂ እንቅስቃሴ ማድረግ ያለበት ተማሪዉ ነዉ። ይህንን ያልተቀበለና ያልተከተለ መምህር በተግባር ተፈላጊዉን የባሕርይ ለዉጥ በተማሪዉ ሕይወት ለማምጣት አይችልም። ተማሪዎች ያለፍርሀት በነፃነት የሚሰነዝሩት ሀሳብ፥ የሚጠይቁት ጥያቄ፥ የሚያካሂዱት ዉይይት በመምህሩ መለኪያ ሳይናቅ መበረታታት ይሮርበታል።

## የጎልማሳነት /ኮረዳነት/ ዕድሜ 13/14/-19/20 ዓመት ባሕርያትና የመምህሩ ሚና

ልጆች ዕድሜአቸዉ እየጨመረ ሲሄድ የአካል መዳበርና የአእምሮ ብስለት እያገኙ የተለያዩ የባሕርያት ለዉጥ እንደሚያሳዩ ይታወቃል። በተለይ ከልጅነት ወደጉርምስናና ኮረዳነት የሚደረግ ሽግግር በልጆች ባህርይ ላይ የሚያስከትለዉን ለዉጥ ይህም በትምህርቱ ሂደት የሚኖረዉን አዉነታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ። ይህንን በሚመለከት ዋና ዋና ሀሳቦች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል።

ከልጅነት ወደ ጉርምስናና ኮረዳነት የመሸጋገር ሂደት በአካላዊና ስሜታዊ ለዉጦች የተጎዳኘ በመሆኑ ይህ አዲስና ፈጣን ክስተት በባሕርያቸዉ ላይ ከፍተኛ ለዉጥ ያስከትላል። የመደሰትና ወዲያዉ ደግሞ የመከፋት፥ የማኩረፍ፥ የመጠርጠር ራስን በተወሰነ ደረጃ የመቀበልና ያለመቀበል፥ ወዘተ ስሜቶች በመፈራረቅ ይከሰታሉ። በዚህ ዕድሜ ክልል ያሉ ተማሪዎች በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የጎላ የጤና ችግር ባይታይባቸውም የእንቅልፍ ጊዜ መዛባትና የምግብ ፍላጎት መቀነስ ይታይባቸዋል። በመካከላቸዉ ለሚፈጠረዉ የተቃራኒ ፆታዎች መሳሳብና መፈላለግ በአካል ዕድገት ዝግጁ ቢሆኑም በልምድና በሥነ-ልቦና ረገድ ገና ጥሬና አዲስ መሆናቸዉ ትልቅ ፈተና ይሆንባቸዋል። በእነዚህና በመሳሰሉት ሁኔታዎች የተነሳ አንዳንድ ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ ግራ የገባቸዉ ቢመስሉ የሚደነቅ አይደለም። ሁኔታዉ የትምህርት ተሳትፎአቸዉን እስከተወሰነ ደረጃ ሊቀንስ ይችላል።

መምህሩ እነዚህን ሁኔታዎች በመገንዘብ የተማሪዎችን ትኩረት መሳብ በሚችል መልኩ የትምህርቱን አቀራረብና የራሱን ግንኙነት ለማሻሻል መጣር ይኖርበታል።

ከባሕርያቸዉ አኳያ ሲታዪ ወጣት ተማሪዎች ለት/ቤት ደንብና ለቤተሰብ ስርዓት ከመገዛት ይልቅ በጓደኞቻቸዉና መሰሎቻቸዉ ዘንድ ተቀባይነትንና አድናቆትን በሚያስገኙላቸዉ ተግባራት ላይ መሳተፍ ይቀናቸዋል። አነጋገር፣ አለባበስ፣ መልክ፣ ቁመና፣ የትምህርት ችሎታ ወዘተ ብዙ ጊዜ ትኩረታቸዉን የሚስቡ ጉዳዩች ናቸዉ። በዚህ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎችን በክፍል ተሳትፎአቸዉ ሆነ በተለያዩ ትምህርት ነክ ሥራዎች የተነሳ በጓደኞቻቸዉ ፊት ሆነ በግላቸዉ ከማንቋሸሽ መቆጠብ ያስፈልጋል። ስብዕናቸዉን የሚነካና የሚያዋርድ ማንኛዉም ዓይነት አስተያየትና ድርጊት ከመምህሩ እንዳይኖር ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል። በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ በመምህሩና በተማሪዎች መካከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶች እነዚህን ጉዳዩች ማገናዘብ ይኖርባቸዋል።

በጉርምስናና በኮረዳነት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት አካባቢ በወላጆችና በልጆቻቸዉ እንዲሁም በመምህራንና በተማሪዎች መካከል የሚፈጠሩ ተደጋጋሚ ግጭቶች በተለይ ከመንስኤዎቻቸዉ ጋር መታወቅ ይኖርባቸዋል። ልጆች ጎረመስን ሲሉ ወላጆች ሆኑ መምህራን እንደልጅ የሚቆጥሩአቸዉ አጋጣሚዎች ብዙ ናቸዉ። ገና ብዙ እንደሚቀራቸዉና ብቁና ሙሉ ሰዉ እንዳልሆኑ በተለያየ መልኩ ይነገራቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ከእንግዲህ ልጅ አይደለህም (ሽም) ይህንና ያንን ማድረግ ይጠበቅብሀል (ሻል) የሚሉ አስተያየቶች ይቀርቡባቸዋል። ልጆቹ መሆንና ማድረግ ያለባቸዉንና የሌለባቸዉን በግልጽ ተለይቶ ስለማይቀርብላቸዉ በሁኔታዉ ግራ ይጋባሉ። በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች በልጅነታቸዉ ወቅት ሲደረግ የነበረዉን የወላጅና የመምህር የቅርብ አመራር፣ የበላይነትና ወሳኝነት በአብዛኛዉ በተዘዋዋሪ መልክ ይቃወማሉ። ከእንግዲግ ለእነርሱ የሚበጀዉን ራሳቸዉ መወሰን እንደሚችሉና እንደልጅ መታየት እንደሌለባቸዉ በተለያየ መልክ ይገልጻሉ። ሆኖም የወላጅና የመምህር የተለመደ ክትትል እስከተወሰነ ደረጃ ስለሚቀጥል ሁኔታዉ አልፎ አልፎ አለመጣጣምንና ግጭትን ያስከትላል።

በመሠረቱ ተማሪዎቹ ስለራሳቸዉና ከሌሎች ጋር ስላላቸዉ ግንኙነት የሚያሳዩት አዲስ አመለካከት ጤናማና መበረታታት ያለበት ነዉ። በራሳቸዉ የማሰብ፣ ያሰቡትን በተግባር የማዋል፣ ከሌሎች ሰዎች ጥገኝነት ነፃ ወጥቶ ራሳቸዉን በራሳቸዉ የመምራት ፍላጎት እጅግ ጠቃሚ ነዉ። በዚህ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች በተለይም 20 ዓመት ሲጠጉ በአካል፣ በአእምሮ፣ በስሜታቸዉና በማኅበራዊ ግንኙነታቸዉ በአብዛኛዉ ወደ ሙሉ ሰዉ የሚጠጉ መሆናቸዉን መምህሩ ሊገነዘብ ይገባል። ግንኙነቱንም ከዚሁ አኳያ ማስተካከል ይጠበቅበታል።

በተማሪዎች ሕይወት ተፈላጊዉን የባሕርይ ለዉጥ ለማምጣትና ዕድገታቸዉን ለማፋጠን ት/ቤቶች በሚያደርጉት ጥረት ላይ ጎጂ ተፅዕኖ ከሚኖራቸዉ ነገሮች አንዱ ባሕል ነዉ። በአገራችን ኢትዮጵያ ሆነ በሌሎች አገሮች የባሕል አሉታዊ ተፅዕኖ ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ የጠነከረ ነዉ። ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ትርፍ ጊዜያቸዉን በቤት ዉስጥ ሥራዎች ያሳልፋሉ። በቂ የጥናት ጊዜ የላቸዉም። ሴት ልጅ ዝምተኛ እንድትሆን በሚያዘዉ በኅብረተሰብና በቤተሰብ ተፅዕኖ የተነሳ

በትምህርት ወቅት ያልገባትን ጠይቃ ለመረዳት የምታደርገዉ ጥረት ዉ/ን ነዉ። በዚህና በመሳሰሉት ተፅዕኖዎች የተነሳ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን አጠናቀዉ ተሳክቶላቸዉ የከፍተኛ ትምህርት ዕድል የሚያገኙና በሥራ የሚሰማሩ በቁጥር በጣም ጥቂት ናቸዉ። ለዚህ ዕድል ያልታደሉ አብዛኞዎቹ ሴቶች ቀሪ ሕይወታቸዉን የሚያሳልፉት በተመሰቃቀለና አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ነዉ። ከዚህ አጭርና ጠቅለል ብሎ ከቀረበ የሴቶች የትምህርትና የኑሮ ሁኔታ መምህሩ ብዙ ሊገነዘብ የሚገባዉ ጉዳይ አለ። በመሰረቱ ሴቶች የባህል ተፅዕኖ ከሌለባቸዉና ምቹ የትምህርት ሁኔታ ከተፈጠረላቸዉ እንደማንኛዉም ወንድ በትምህርታቸዉ ንቁ ተሳትፎ እንደሚኖራቸዉና ከፍተኛ ዉጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉ መታወቅ ይኖርበታል። ከፍ ብሎ እንደተገለጸዉ በተለያዩ ተጽዕኖዎች የተነሳ ሴቶች በትምህርት ሂደት የሚኖራቸዉ ተሳትፎ ዉስን ሊሆን ስለሚችል ጥያቄ በመጠየቅ፥ መልስ በመመለስ፥ አስተያየት በመስጠት፥ በቡድን ሥራዎች በማሳተፍ ያለመሰልቸት ማበረታታት ያስፈልጋል። ጥረታቸዉን ማድነቅና ችግራቸዉን መረዳት ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ የትምህርት ተሳትፎአቸዉ ሊቀንስና ተስፋ ሊቆርጡ ይችላሉ።

አንድ መምህር መገንዘብ ያለበት ሌላዉ ጉዳይ በትምህርት አቀባበል ችግር ያለባቸዉንና የፈጣን ተማሪዎችን ጉዳይ ነዉ። የትምህርት አቀባበል ችግር ያለባቸዉ ተማሪዎች ከሌሎች ፈጣንና ጎበዝ ተማሪዎች ጋር እኩል እንዲሳተፉ ከተጠበቀ ሁኔታዉ ልጆቹን ከማስጨነቁም በላይ ተስፋ እንዲቆርጡና ትምህርትንም ሆነ ራስን እንዲጠሉ ሊያደርግ ይችላል። በአንፃሩ ግን በተማሪዎች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ የሚችሉ ልዩነቶች ታዉቀዉ በራሳቸዉ ፍጥነት እንዲማሩ ቢደረግና መልካም ዉጤት ሲያሳዩ ደግሞ ከመምህሩ አድናቆት ባይነፈጋቸዉ የበለጠ የመማር ፍላጎታቸዉ ሊጨምር ይችላል። የጥናት ማቴሪያሎችን በመምረጥ፥ በጥናት ፕሮግራም ዝግጅት በመርዳት፥ ከብደዉ የሚታዩትን ርዕሶች በማብራራት፥ የምክር አገልግሎት በመስጠት ወዘተ የትምህርት አቀባበል ችግር ያለባቸዉን ልጆች መርዳት ይቻላል። በተጨማሪም በክፍል ዉስጥ ቀላል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተሳትፎአቸዉን ከፍ ማድረግ ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ልዩ ተሰጥኦና ፈጣን የመማር ችሎታ ያላቸዉ ተማሪዎች የመምህሩን የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እንደሚሹ መታወቅ አለበት። በክፍል ተሳትፎአቸዉና በፈተና ዉጤታቸዉ ከአብዛኞዎቹ ልጆች የጎላ ልዩነት የሚያሳዩ ልጆች ተለይተዉ ታዉቀዉ ለበለጠ ሥራ ሊበረታቱ ይገባል። እንደነዚህ ዓይነት ልጆች በትርፍ ጊዜያቸዉ በሥነ-ጽሑፍ ዉድድሮች፥ በድራማዎች፥ በሥዕል ሥራዎች ወዘተ እንደየዝንባሌአቸዉ እንዲሳተፉ ማድረግ ጊዜአቸዉን ጠቃሚ ተግባር ላይ እንዲያዉሉ ያግዛል። ጎበዝ ተማሪዎች ስላላቸዉ ችሎታና ልዩ ተሰጥኦ ወላጆቻቸዉን ት/ቤት በመጋበዝ ዉይይት ማድረግና ወላጆች አቅማቸዉ በፈቀደ ሁሉ ለልጆቻቸዉ ተገቢዉን ድጋፍ እንዲሰጡ ማበረታታት ይጠቅማል።

## ማጠቃለያ

የአንድ መምህር ብቃት የሚለካዉ ከሚያስተምረዉ ትምህርት ዕዉቀት ባሻገር የተማሪዎቹን ባሕርይ በመረዳት የትምህርቱን ሂደት ዉጤት /የባሕርይ ለዉጥ/ ለማስገኘት በሚችል መልኩ መምራት በመቻሉ ነዉ። የተማሪዎቹን ሥነ-ልቦናዊ፥ አካላዊ፥ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት በበቂ ሁኔታ መረዳት አስቸጋሪ ሥራ ቢሆንም አማራጭ የሌለዉና የማይታለፍ ጉዳይ ነዉ። በመሆኑም ከልጅነት እስከ ጉርምስናና ኮረዳነት ባለዉ የዕድሜ ክልል ጎልተዉ የሚታዩትን አበይት የባህርይ ለዉጦች ጠንቅቆ ማወቅ አስፈላጊ ነዉ። ቀደም ሲል እንደተገለፀዉ ልጆች በአካልና በአእምሮ የሚያደርጉት ፈጣን እንቅስቃሴ፥ የማረፍና የመዝናናት ፍላጎት፥ የመታወቅ ፍላጎት፥ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ለማዳበር ያላቸዉ ፍላጎት፥ ነፃና ተጽዕኖ የሌለዉ የትምህርት አካባቢ ለማግኘት ያላቸዉ ፍላጎት፥ በጉርምስናና ኮረዳነት መጀመሪያዎቹ ዓመታት የሚከሰቱ ግራ የመጋባት ሁኔታዎችና አልፎ አልፎ ከቤተሰብና ከት/ቤቶች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች፥ በተለይ በሴት ልጆች ላይ የሚደረገዉ የባሕል ተጽዕኖ ጉዳይ፥ የትምህርት አቀባበል ችግር ያለባቸዉ ተማሪዎች ሁኔታ፥ ለፈጣንና ጎበዝ ተማሪዎች የሚደረግ ልዩ ትኩረት ወዘተ ጉዳዮች ቢያንስ በዋና ዋና ሀሳብ ደረጃ ለመምህሩ ግልጽ ሊሆኑ ይገባል። መምህሩ በእነዚህና በመሳሰሉት ከተማሪዎች ባሕርይ ጋር በተያያዙ ትምህርት ነክ ጉዳዮች ላይ የሚኖረዉ ዕዉቀት በመማር ማስተማር ሂደትና በትምህርቱ ዉጤት ላይ የጎላ ልዩነት እንደሚያስከትል ይታመናል። በመሆኑም መምህሩ በዚህ ረገድ ያለዉን ዕዉቀት ከፍ ለማድረግ ያማያቋርጥ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

## References


Biehler, Robert, Snowman and Jack (1986). Psychology Applied to Teaching. 5th ed. Boston: Houghton Mifflin Company.

Child, Dennis (1986). Psychology and the Teacher. 4th ed. London: Cassell Educational Ltd.


Clifford and Margaret (1981). Practicing Educational Psychology. Boston: Houghton Mifflin Company.

Gage, Berliner and Davis (1988). Educational Psychology. 4th ed. Boston: Houghton Mifflin Company.

FACTS AND FIGURES

## IER LIBRARY

IER Library serves about 50-80 readers a day. It has rare educational documents which are not available elsewhere. This year the Library obtained mor than 300 new books and docummments. The library has become an important resource center for post-graduate and undergraduate students of the Faculty of Education.



A section of IER-Library - all readers are busy - reading and writing ... what about the Librarian?